# የ COVID-19 የመስመር ላይ የጉዳይ ምርመራ ጥናት ግልባጭ/ትራንስክሪፕት

[አዝናኝ ሙዚቃ]

[ትረካ] የጉዳይ ምርመራዎች የ COVID-19 ስርጭትን ለመቀነስ የሚያስችሉ መንገዶች ናቸው

የሰለጠኑ የጤና ሰራተኞች በ COVID-19 ከተያዙ ሰዎች ጋር ይገናኛሉ እናም በቅርበት ከእነርሱ ጋር ጊዜ ያሳለፉ ሰዎችን ለማግኘት ጥያቄዎችን ይጠይቋቸዋል ። እነዚህ የቅርብ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች COVID-19 ሊኖርባቸው ስለሚችል ቤት መቆየት ይኖርባቸዋል ።

ብዙውን ጊዜ የጉዳዩ ምርመራ ቃለ መጠይቅ በስልክ ይከናወናል ። አሁን በግል ፣ በድረገፅ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን የመመለስ አማራጭ አለዎት ።

ምርጡ ነገር? ሲመረመሩ የሞባይል ስልክ ቁጥርዎን ካጋሩ የዳሰሳ ጥናቱን መውሰድ እንደሚችሉ ለማሳወቅ በአጭር ጽሑፍ መልእክት እንልክልዎታለን!

በመጀመሪያ ፣ እኛ እርስዎን እናገኝዎታለን። የበለጠ ምቾት በሚሰማዎት ቋንቋ ላይ በመመርኮዝ 1 ፣ 2 ፣ 3 ወይም 4 በማለት ምላሽ መስጠት ይችላሉ ። የኢሜይል አድራሻዎን እንጠይቅዎታለን እና የዳሰሳ ጥናቱን አገናኝ(ሊንክ) በቀጥታ ወደ የመልዕክት ሳጥንዎ እንልክልዎታለን ። ለጽሑፉ ምላሽ ካልሰጡ ከጤና ሰራተኛ ስልክ ይደወልልዎታል ።

የዳሰሳ ጥናቱን ለመሙላት ጊዜ መውሰድ ይችላሉ ። በመጨረሻ ፣ COVID-19 ን ለሌሎች የማስተላለፍ አደጋን እንዴት መቀነስ እንደሚችሉ አስመልክቶ እንዲሁም እንደ ግሮሰሪ እና መድኃኒት ላሉ ነገሮች ለእርስዎ ተደራሽ ሊሆኑ የሚችሉ በአቅራቢያዎ ስለሚገኙ ግብአቶች ዝርዝር አስፈላጊ መረጃዎችን ይቀበላሉ።

የጤና መምሪያው ግላዊነትዎን በጣም አጽንኦት ሰጥቶት ይመለከታል። ገንዘብ ፣ የባንክ መረጃ ወይም የማህበራዊ ደህንነት ቁጥርዎን በጭራሽ አንጠይቅም ።

የምርመራ ውጤትዎ ፖዘቲቭ ከሆነ እና ጥያቄዎች ካሉዎት ከጤና ሰራተኛ ጋር ለመነጋገር በ 651-201-5689 ላይ መደወል ይችላሉ ።

[አዝናኝ ሙዚቃ]

Minnesota Department of Health
Communications Office
PO Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
651-201-4989
health.communications@state.mn.us
www.health.state.mn.us

1/28/21 (Amharic)

*ይህንን መረጃ በተለየ ቅርጸት/ፎርማት ለማግኘት በስልክ ቁጥር፡ 651-201-4989 ላይ ይደውሉ*